የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 44
ADDIS ABABA 14th July, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፬/፳፻፮ ዓ.ም

ለከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ................ገጽ ፯ሺ፬፻፴፬

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፬/፳፻፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፶ ሚሊዮን ዩሮ (ሃምሣ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፱ ቀን ፳፻፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፰ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

CONTENTS

Proclamation No. 844/2014

Agence Francaise De Developpement Credit Facility Agreement for Financing the Reinforcement of the Power Transmission Network Project Ratification Proclamation ..........................................................Page 7434

## PROCLAMATION No. 844/ 2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AGENCE FRANCAISE DE DEVELOPPEMENT

WHEREAS, Credit Facility Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Francaise De Developpement stipulating that the Agence Francaise De Developpement shall make available to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit facility in an amount of fifty million EURO (EURO 50,000,000) for financing the reinforcement of the Power Transmission Network Project was signed in Addis Ababa, on the 19th day of December 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of June 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2•30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ማጠናከሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፬/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር CET 1047 01 V የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶ ሚሊዮን ዩሮ (ሃምሣ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agence Francaise De Developpement Credit Facility Agreement for Financing the Reinforcement of the Power Transmission Network Project Ratification Proclamation No 844/2014.

2. **Ratification of the Agreement**

The Credit Facility Agreement signed in Addis Ababa, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Francaise De Developpement on the 19th day of December 2013 Agreement No CET 1047 01 V is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit Facility amount of Fifty million EUROS (EURO 50,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Facility Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of July, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**